# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 2 ቁጥር 1 መስከረም ፮ ቀን ፪ ሺ ፲ ዓ.ም.

## ኢትዮጵያዊነትንና የዓላማ ጽናትን እናውርስ

(ጽሁፉን በድምጽ ቅጂ ለማድመጥ እዚህ ይጫኑ https://www.youtube.com/watch?v=OaxFuUkM3XQ)

ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን ለአዲሱ ዓመት 2010 ዓ.ም. በሰላም አደረሳችሁ በማለት ከ "***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን)***" የመስከረም ዕትማችንን እናስነብባለን። የመስከረም ወር ለእኛ ለ"***ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" ደግሞ የልደታችን ወር በመሆኑ ለአንደኛ ዓመት ክብረ በዓላችን እንኳን አደረሳችሁ እንላለን። መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. (September 18, 2017) እራሱን ለሕዝብ ይፋ ያደረገው "***ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" ለኢትዮጵያ ሀገራችን የግዛት ሉዓላዊነትና ለሕዝባችን አንድነት ድምፃችንን በማሰማት የተያያዝነው ሀገር አድን ትግል እነሆ! አንድ የትግል ምዕራፍ አገባዶ ወደ ሁለተኛው ተሸጋግረናል።

***ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!***

"***ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" በአሳለፍነው አንድ የትግል ዓመት ምን አድርገን፣ ምን ሠርተን አለፍን? ጠንካራና ደካማ ጎኖቻችንን ገምግመን ለቀጣዩ የትግል ዓመት ስንነሳ የትግል ዓመትን ለመቁጠር ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሀገሩ ባለቤትነት የሚበቃበትን ጊዜ ለማሳጠር ጭምር ነው።

- ለ27 ዓመት በወያኔ/ኢሕአዴግ ጣምራ አፈና እየተረገጠ ላለው ሕዝባችንና እየተዳከመች ላለችው ሀገራችን መፍትሄው አንድነት መሆኑን ለማስረገጥ "***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ!***" ብለን ተነስተናል።
- ለ27 ዓመት በዘረኛው ወያኔ/ኢሕአዴግ የዘር ፖለቲካና ከፋፍለህ ግዛ እየታመሰች ላለችው ሀገራችን መፍትሄው ኢትዮጵያዊነትን ከፍ በማድረግ መሆኑን ለማጉላት "***ኢትዮጵያችን***" ብለን ተነስተናል።
- ለ27 ዓመት የተደረገው ፀረ-ወያኔ/ኢሕአዴግ ተጋድሎ ለዘረኛው አገዛዝ እንዲያመቸው በአንድ በኩል በዘር ተከፋፍሎ መደራጀቱ በሌላ በኩል የጋራ አጀንዳ ይዞ የተናጠል ጉዞ የትም አያደርስምና በጋራና በኅብረት ትግሉን ከግብ ለማድረስ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ባካተተ መልኩ ለመንቀሳቀስ ያመች ዘንድ "***ሕዝባዊ ንቅናቄ***" ብለን ተነስተናል።

***ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!***

"***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ዳግም እንዲያብብ ካለን ያልተቋረጠ ጥረት አንጻር ባሳለፍነው አንድ ዓመት ለሕዝብ ያበረከትናቸውን ጽሁፎች በድረ ገፃችን (www.ethiopiachen.org) ቢካተቱም ዳግም እያስታወስናቸው በአሁኑ

እትማችን መልዕክታችንን ለአንጋፋ ኢትዮጵያውያን ታጋዮች፣ ሀገር ወዳዶችና ምሁራን እንዲሁም ለሁሉም ፖለቲካ ድርጅቶች አድርገናል። ለኢትዮጵያ ህዝብ የድል ባለቤትነትና ለሀገራችን ደህንነት እስከታገልን ድረስ "*ቢጋራ እንፋለም፣ አዲሱን ትውልድ ቦታ እንስጠው*" ስንል የምናሰማው ድምጻችን፣ የምናስነብበው ትንታኔአችን እነሆ!

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከማይፈታ አዙሪት ውስጥ ከወደቀ እነሆ ከግማሽ ምዕተ ዓመት በላይ ሆነ። በተለይ ዘውዳዊው የዓፄ ኃይለስላሴ መንግሥት ወድቆ አምባገነናዊው የወታደር መንግሥት ደርግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የፖለቲካ ሽኩቻ ጣራ የነካበት ---ለአንድ ትውልድ እልቂት ምክንያት የሆነ--- ኢትዮጵያ ሊያሳድጓት፣ ሊያበለጽጓት፣ ሕዝቧን ለእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ነፃነት ሊያጎናጽፏት ቆርጠው የተነሱ ልጆቿን ያጣችበት አሳዛኝ የታሪክ ጠባሳ ሆኖ አልፏል። ከደርግ ውድቀት ማግሥት በኋላ ደግሞ "ከድጡ ወደማጡ" እንዲሉ የዘር ፖለቲካ ሀገሪቱን ነቀዝ እንደበላው እንጨት ውስጥ ውስጧን በልቶ እንደ ሀገር እንዳትቀም ጉልበት አሳጥቷት ይገኛል።

ይህ ሁኔታ የማያስጨንቀው ኢትዮጵያዊ የለም። በየትኛውም ቦታ በተናጠል ሲገናኝ የሀገሩ ጉዳይ በእጅጉ እንደሚያሳስበውና እንደሚያስጨንቀው ይናገራል፣ ያወራል፣ ይከራከራል። አክራሪ ዘረኞች እንዳሉ ሆነው እምዬን ባዩ፣ ለሕዝብ የ"ገደል ማሚቶ" የሆነው ኃይል፤ የችግሩ ጥልቀት ከገባው ታድያ እንዴት ከ50 ዓመት ለበለጠ ጊዜ ለችግሩ መፍትሄ ሳያገኝ ቀረ?

እኛነታችንን አበክረን ስንመለከተው እኛ ኢትዮጵያውያኖች በጠረጴዛ ዙሪያ ሆነን መብላትና መጠጣት እናውቃለን። በክብ ተቀምጠን መጠጥ እየጠጣን ቧልት ጨዋታዎችን እየተጫወትን መሳሳቅ እንችልበታለን። በለቅሶው እንደ ባህላችንና ሃይማኖታችን መለስተኛ መለያየት ቢኖርም፣ ዛሬ የኑሮ አቅም ቢለውጠውም እስከ አርባ በጋራ እናስተዛዝናለን። የዕዝን ወስደን በጋራ እናስተዛዝናለን። በሠርጉ እህቶቻችን በጋራ ደግሰው፣ በአንድላይ ጨፍረው ወንድሞች በጋራ ድንኳን ጥለው፣ ሙሽራና ሙሽሪትን አጅበው፣ "ሃይ ሎጋ! ሃይ ሎጋ! ሆይ!" ብለው ይድራሉ። ቡናና የቡና ቁርስ እኮ ካለጐረቤት አይታሰብም። በየገጠሩ የደቦ እርሻ፣ የጋራ ባህላዊ ዝማሬዎች፣ መረዳዳቶች፣ ለችግር ጊዜ "ሞረሽ" መባባል የተለመደ ነው። ጐረቤት ሲታመም ፈጥነን ደራሽ፣ ተጋግዘን አስታማሚና ጠያቂ ነን። በጥቅሉ ልቅሷችንና ሳቃችን፣ ሀዘንና ደስታችን፣ እስላምና ክርስቲያንነታችን፣ ወዘተ በጋራ መረዳዳትና መፈቃቀር ላይ የተመረኮዘ አኩሪ ባህል ነው ያለን። እውን ዶሮን ከነልጁ (እንቁላል) በአንድ ማዕድ የምንጋራ እኛ ብቻ መሆናችንን እናውቀዋለን? የመጐራረስ ባህላችንስ ከእኛ ሌላ ማን አለው? የራሳችንን ጥለን የፈረንጅ Thanksgiving ስናደንቅ የእኛን በፋሲጋ ከጐረቤት ተጠራርቶ አብሮ መብላት አልረገጥነውምን? የውጣውጥ ቦርዴ፣ የኦሮሞ ጠላ በአንድ ሽክና በጋራ እንደሚጠጣ እናውቃለን? ሌላም ሌላ።

ወደ ፖለቲካው መድረክ ስንመጣ ግን በሰከነ መንፈስ አንወያይም። እንደተማረ ሰው በውይይት ለሀገር የሚጠቅመውን ሀሳብ ወስደን አንድ ላይ ከመስራት ይልቅ "ለምን የኔ ሀሳብ ተቀባይነት አላገኘም" ብለን የምናኮርፍና ካዚያ በኋላ የተለየ ሀሳብ ያለውን ሰው በጠላትነት የምንመለከት ብዙዎች ነን። "የኔ ካልሆነ" የሚል ግትር አቋም የብዙዎች ኢትዮጵያውያን በሽታ ሳይሆን አይቀርም። የሌላው ሰው ሀሳብ የበለጠ ለሀገርና ለወገን ጠቃሚ መሆኑን ብናውቅ እንኳ ያን የተለየ ሀሳብ ተቀብሎ ከማስተናገድ ይልቅ ጦር ብንማዘዝ የምንመርጥ ጥቂቶች አይደለንም። ለዚህ ሳይሆን አይቀርም ችግራችን አንድ ሆኖ ሳለ በአንድ መሰባሰብ ያቃተን።

ለማሳያ ያህል ያለፉትን ድርጅቶች ብንመለከት እንኳን (ደርግ፣ መኢሶን፣ ኢሕአፓ፣ . . .) ባሳለፍናቸው ረጅም የትግል ዓመታት የትኛው ድርጅት በዚች አገር ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣

እድገትና ብልጽግና እንዲመጣ፣ ያለምንም ክፍያ አንድያ ህይወቱን ሊሰዋ እንደተነሳና እንደ ደከመ ለታሪክ ምስክርነት መተው አቅቶናል። ዛሬም "የእኔ ድርጅት ትክክል ነው፣ ጥፋቱ ሁሉ የሌላው ድርጅት ነው" በሚል ጣት የመጠቋቆም ድርጅታዊ አምልኮ በመታወር ሲሟገቱና የጎሪጥ ሲተያዩ መኖር በእጅጉ የሚያሳዝን ነው።

ባሳለፍናቸው የግማሽ ምዕተ አመት የተመሰቃቀለ የፖለቲካ ጉዞ ለኢትዮጵያ የሚጠቅምም ሆነ የማይጠቅም፣ ክፉም ሆነ ደግ፣ አልሚም ሆነ አጥፊ፣ ታሪክ ይዘክረዋል። ሁሉንም ለታሪክ መተው ይገባል። ወጣቱ ትውልድ ከአንጋፋው ትውልድ በጥንካሬው ኩራትን፣ የበለጠ ጥንካሬን እንዲወስድ፤ ከድክመቱና ከውድቀቱ ደግሞ ትምህርት ወስዶ የራሱን መንገድ አስተካክሎ እንዲሄድ መርዳት የእያንዳንዱ አንጋፋ ትውልድና ምሁራን ሃላፊነት ነው። ይህንን ባለማድረግ ባለፈ ታሪክ ተቀፍድዶና ተይዞ መጭው ጊዜ ብሩህ እንዳይሆንና የጨለማ ጉዞ እየሆነ እንዲጓዝ የምናደርገው ግትርነት ለሀገርና ለሕዝብ ሲባል ሊመረመር ይገባዋል። በተለያየ አጋጣሚ በግለሰብ ደረጃ፣ በቡድንም ይሁን በፖለቲካ አለመግባባት የተከሰቱ ሽኩቻዎችን፣ መለያየቶችን ለሀገርና ሕዝብ ሲባል መናናቅ እንቅፋት ነውና ይቅር ባይነትን ልንቀበል ይገባናል። ለሕዝብና ለሀገር ነፃነት ሲባል የራቁንን ማቅረብ፣ የተለዩንን መሰብሰብ፣ ጀርባችንን የሰጠናቸውን ማቀፍ ትልቅነት ነው። በጥናት ባይረጋገጥም ለዚህ ሁሉ የዳረገንን፣ በአንድ መድረክ እንዳንታገል እንቅፋት የሆነውን "አልሸነፍም" ባይነት ክፉ ልክፍት አውልቀን መጣል ይኖርብናል።

ዛሬ ወያኔ/ህወሀት/ኢሕአዴግ አገሪቱን በዘር ከፋፍሎ በጐረቤት አፍሪካ ሀገር እንዳየናቸው ሊያደርገን በሚራራጥበት ጊዜ ዕድሜ ጠገብ የትላንትናዎቹና ሀገር ወዳድ ምሁራን በአንድ ተሰባስበው ምን የፈየዱት ነገር አለ? ያለፈውን የሀገር ውድቀትና የትውልድ እልቂት ለታሪክ ትተነው መጭውን በማሰብ ለመሰባሰብና አንድ ላይ ለመስራት ለምን ከበዳቸው? የማይገባ ነገር ነው። እንዲያውም ዱሮ ከነበረን ለግድያ የመፈላለግ ስሜት ዛሬም በእርጅናው ቁልቁለት ላይ ሆነን ከዚያው የመጠፋፋት አዙሪት ውስጥ የወጣን አንመስልም ቢባል መስካሪው ተግባር ነው። የምናካሂደው የፖለቲካ ትግል እስከሆነ ድረስ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር አይደለም በአንድ ድርጅት ውስጥ በሃሳብ መፋጨት፣ መጨቃጨቅ፣ መነጋገር፣ መከራከር አኩሪ ልምድ መሆን ይኖርበታል። ***<u>የተለያዩ ሃሳቦች ፍጭት ነው የሃሳብ ነፃነትን አስረግጦ አመርቂ አመራር የሚሰጠው።</u>*** አለዚያማ "ከእጅ አይሻል ዶማ" ቢተረትብን ልንደነቅ አይገባም።

***ውድ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን!***

ሀገር በጽኑ ታምሳለች፣ ተበጥብጣለች። የ"አድኑኝ" ጩኸቷን እያስተጋባች ነው። ይህንን በጥባጭ፣ ይህንን አማሽ ከስሩ ነቅሎ የሚጥል ልብ ያለው ጠንካራ ልጅ---ጠንካራ ትውልድ እየጠራች ነው። ለዚህ ደግሞ ያለፈውን ሳይሆን መጭውን አሻግሮ የሚመለከት---ከአለፈ ልምዱ ተነስቶ የሰከነና የበሰለ ምክር ለአዲሱ ትውልድ የሚያስተምር ቀደምት ትውልድ ያስፈልጋል። ያለፈው የክሽፈት ስህተት እንዳይደገም ከተጓዝንበት የትግል ተመክሮ በመነሳት አዲሱን ትውልድ የሚያስተምር አንጋፋ ትውልድና ሀገር ወዳድ ምሁር ግድ ይላል። ያለዚያ ልጆቻችን "ሀገር አልባ" ሊሆኑ ነው። ጠንካራ ትውልድ ይፈጠር ዘንድ ተግቶ የሚሰራ የሁሉም የዚያ ዘመን ትውልድና የምሁራን ሃላፊነት ነው ብለን "***አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***" በዚህ አዲስ ዓመት 2010 ዓ.ም. መስከረም ወር በጋራ ለመሰባሰብ ልቦናውን ይስጠን ማለትን ወደድን።

እንዲህ ተበታትነን ነው ከሩብ ምዕተ ዓመት ላላነሰ ሀገር በዘረኛው ህወሀት ከምንጊዜውም በላይ እንድትዋረድና እንድታንስ የተፈረደባት። የእኛ "በዱሮ በሬ ማረስ"ና አንድ አለመሆን በተዘዋዋሪ

መንገድ ቢሆንም ለህወሀት የጥፋት ተልኮ ተባባሪ ሆነናል። ችግሩ አንድ ዓላማ ይዘን ግና ሺህ ቦታ ተበጣጥሰን በእውቀትም በችሎታም በምንም መስፈርት ሀገር ለማስተዳደር ብቁ ያልሆኑ ሰዎች ገዥ ሆነው በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጥባጥቤ እየተጫወቱበት ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ ዛሬ የገባችበት ከፍተኛ የሀገር ውድቀትና የዜጎቿ ውርደት፣ እንግልት፣ ስደት፣ እስር፣ ረሃብ፣ ሞት… ሽማግሌ ሆኖ ሊያስታርቀንና ሊያስተባበረን ካልቻለ ከቶ ምን ቢፈጠር ይሆን አንድ ላይ መቆም የምንጀምረው? ሁላችንም በየፊናችን በተናጠል ሮጠን ደግሞ ወያኔን ያህል በዘረፋ ኢኮኖሚውን አጠናክሮ፣ በየትኛውም ቦታና በየትኛውም ድርጅት ውስጥ የስለላ መረቡን ለመዘርጋት የሚችል የማፊያ ቡድን በቀላሉ ማንበርከክ አይቻልም። አሁን ባለውና በሚታየው የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ከህወሀት የበለጠ ለኢትዮጵያችን አጥፊ የሆነ ቡድን ደግሞ የለም። ለወደፊቱም አይመጣም። የእኛ ለኢትዮጵያ ሀገራችንና ለሕዝባችን የምንቆረቆር ወገኖች መለያየትና አለመተባበር ግና ዛሬም ወደፊትም አጥፊ ጠባሳ ጥሎ እንደሚያልፍ መናገር እውነትነት አለው። የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና ምሁራን ተስማምተውና ተደጋግፈው በጋራ ሕዝባዊ ትግሉን አቅጣጫ ለማስያዝ ቁርጠኝነትን ካላሳዩ ግና በወያኔ ምሬት በሚነሳው ሕዝባዊ ዓመጽ በሚከፈተው ቀዳዳ ሌላ “ጅብ” የማይገባበት ምክንያት አይኖርም። ከዘረኛው ወያኔ/ኢሕአዴግ ባላነሰ ኢትዮጵያን ለመበታተን ጊዜና አጋጣሚ የሚጠብቁ ለመኖራቸው የአደባባይ ምስጢር ነውና።

## *ወድ የኢትዮጵያ ሀገር ወዳዶች ሆይ!*

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከመቼውም ጊዜ በላይ ነቅቷል። የወያኔ ነገር በቅቶታል። አፈናው፣ እስሩ፣ እንግልቱ መሮታል። የኑሮ ውድነቱ አንገፍግፎታል፤ የውሸት ፕሮፓጋንዳው አስጠልቶታል። ከሁሉም በላይ የወያኔ ማናለብኝነትና የጥጋብ እብሪት ከሚሸከመው በላይ ሆኖበታል። በየአቅጣጫው በአገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሕዝባዊ እምቢተኛነቱን አሳይቷል። ሆኖም ግን  ለድል አልበቃም። ምክንያቱም እነዚህን ሕዝባዊ አመጾች በአንድ አቀናጅቶ የሚመራ ጠንካራ ድርጅት አላገኘም። በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ የተጠናከረ ድርጅት ባለመኖሩ የተጀመሩ ሕዝባዊ አመጾች ሁሉ በወያኔ ተጠልፈው ቀርተዋል። ጠንካራ ድርጅት ቢኖር ኖሮ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ተጀምሮ የነበረው ሕዝባዊ እምቢተኛነት ተጠናክሮ ሀገር አቀፋዊ መልክ በያዘ ነበር። ከዚያ በኋላም በየአቅጣጫው ተቀጣጥለው የነበሩ በኢትዮጵያ ኦሮሞ ልጆች፣ በአማራው ወገኖች፣ በጋምቤላ ኢትዮጵያውያኖች፣ ወዘተ. የወያኔን ዘረኛ መንግሥት ያነቃነቁና ያርበተበቱ አመጾች መልክ ይዘው ለድል በበቁም ነበር። ከዚህ የበለጠ ለውጥ ፈላጊ ሕዝብ መቼም አይገኝም። እየሞተ ያለ፣ ብቻውን ያለ ጠንካራ መሪ ትግሉን የቀጠለ። ከዚህ የበለጠም ለውጥን የተጠማ ሕዝብ የታየበት ጊዜ የለም። በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ አሁኑ ጊዜ ሕዝብ ያለማንም ቀስቃሽ ነቅቶና ከፍርሀት ወጥቶ ለውጥ የፈለገበት ጊዜ አልታየም። ይህን ለውጥ የናፈቀን ሕዝብ የሚመራ ጠንካራ ድርጅት ይፈጠር ዘንድ ተበታትነው ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች በጋራ አስማሚ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ መክረው በአንድ መድረክ ይታገሉ ዘንድ ግፊትና ጫና ማድረግ ከሁሉም ኢትዮጵያዊ ሀገር ወዳድ ይጠበቃል። ታጋይ ፖለቲካ ድርጅቶች፣ አንጋፋው ትውልድና የምሁራን ድርሻ ከዚህ አኳያ ምን መሆን አለበት? ነው የ“***ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ***” የአዲስ ዓመት ጽሁፍ መነሻና አንኳር ነጥብ።

1. ይቅር መባባልን፣ ተነጋግሮ መደማመጥንና መቻቻልን በውስጣችን አስርጸን ከግል ስሜታችንና ከድርጅታዊ አምልኮ ወጥተን ለትውልድ የሚተርፍ ተግባር መተግበር ከአንጋፋው ትውልድና ምሁራን ይጠበቃል።

2. እንደሚነገረው ከሆነ ተቃዋሚ ድርጅቶች እንዲሁም ኢሕአዴግንና አጋር ድርጅቶችን ጨምሮ ከ182 ድርጅቶች በላይ በሀገሪቱ ተፈልፍለዋል። ነገር ግን ተቃዋሚ ነን የሚሉት ሕብረብሔር ድርጅቶችም ሆኑ የብሔር ድርጅቶች ከላይ እንደ ተገለጸው የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ አመጽ አስተባብሮ በአንድ ማምጣት አልቻሉም። ይህ የሚያሳየው የተናጠል ትግል ወያኔን ሊያዳክመው እንዳልቻለ ነው። ስለሆነም ይህ የተቀሰቀሰው ሕዝባዊ አመጽ ግቡን እንዲመታ አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ከባድ ሥራና ኃላፊነት አለበት። "***<u>እንዴት በአንድ ቁመን ይሆን ሕዝባዊ አመጽ ለግብ እናብቃው?</u>***" የሚለው የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ አንጋፋው ትውልድና ምሁራን እንዲሁም ታጋይ የፖለቲካ ድርጅቶች በሙሉ ለመልሱ መዘጋጀትና መስራት ይጠበቅብናል።
3. ወጣቱ ትውልድ ከእኛ ከአንጋፋዎቹ የሚማረው ብዙ ነገር ይኖራል። የትግል ልምዳችን ልናካፍለውና ልናቀርበው ይገባል። ሁልጊዜ በሕይወት መኖር የለም። ያደገች፣ የበለጸገች፣ የተሻለችና ዴሞክራሲ የሰፈነባት ሀገር ለዜጎች ሁሉ ለማውረስ በትኩስ የወጣትነት ዘመን የህይወት መስዋእትነት ለመክፈል ቆርጦ የተነሳ ትውልድ ነበራት ኢትዮጵያ። ዛሬም ለሀገር አንድነት ሲባል ትውልዱ ተጠናክሮ ሀገሩን እንዲጠብቅና መኖርያ እንዲኖረው ነባሩ ትውልድና ምሁራን አይዞህ ሊሉት፣ ሊያበረታቱት፣ ልምዳቸውን ሊያካፍሉት ይገባል። የአሁኑ ትውልድ የሀገር ተቆርቋሪነት ሀላፊነቱን ተረክቦ በመሪነት እንዲታገል ከጎኑ መቆም ያስፈልጋል።

ወያኔ ወጣቱን በብዙ ነገር እንዲሞት እያደረገው ነው። በትምህርት ገሎታል። በዘር ጥንስስ ተጠንስሶ ተጠጅቶታል። የሀገር ፍቅር ስሜት ከውስጡ እንዲጠፋ ከተወለደ ጀምሮ ተሰርቶበታል። ገና ከመወለዱ የሱስ ተጠቂ እንዲሆን ተደርጓል . . .። ይህንን ሁሉ መከራ አልፎ ግን ወያኔን የሚታገለው ይኸው አሳረኛ ወጣት ነው። ልንረዳውና አይዞህ ልንለው ይገባል። የመሪነቱን ቦታ እንዲይዝ ልናበረታታው ይገባል። መንገዱን ልንጠቁመው ያስፈልጋል። ለዚህ ሁሉ በየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት የነበርንና ያለን እኛ አንጋፋዎቹ ለሀገርና ለዚህ ተንከራታች አሳዛኝ ትውልድ ስንል ያለፈውን ከንቱ ቁርሾ ትተን ተባብረን እናስተባብረው። መልካሙን የትግል ልምዳችንን እናሳየው። እኛ ከእናት አባቶቻችን የወረስነው የጀግንነት፣ ሀገርና ሰንደቅ ዓላማ አፍቃሪነት አኩሪ ታሪክ ብለን ዛሬም እንደምንኮራ እኛስ ለዚህ ትውልድ ነገና ወደፊት የሚኮራበት መለያየት ሳይሆን አንድነት፣ ጥላቻ ሳይሆን ፍቅር፣ እኔ ሳይሆን እኛ፣ ክልሌ ሳይሆን ሀገሬ፣ ጨርቄ ሳይሆን ሰንደቅ ዓላማዬ የሚሉ ክቡር ኢትዮጵያዊነትንና የዓላማ ጽናትን እናውርስ።

ድል ለለውጥ ናፋቂው የኢትዮጵያ ሕዝብ!!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!
እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!
"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"
መስከረም 6 ቀን 2010 ዓ.ም. (September 16, 2017)

<u>**ማሳሰቢያ ፡**</u>

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- "አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ" በቅርቡ መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com

ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachen